የሰ/መ/ቁ. 36338

ጥቅምት 25 ቀን 2001 ዓ.ም

**ዳኞች**፡- ዓብዱልቃድር መሐመድ

ሐጐስ ወልዱ

ሂሩት መለሰ

ተሻገር ገ/ስላሴ

ሡልጣን አባተማም

**አመልካች**፡- ገ/መስቀል ደመወዝ - ቀረበ

**ተጠሪ**፡- ወ/ሮ አፀደ መኰንን - ቀረበች፡፡

መዝገቡን መርምረን የሚከተውን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

**<u>ፍ ር ድ</u>**

ለሰበር አቤቱታው መነሻ የሆነው ጉዳይ በሁከት ይወገድልኝ የክስ መነሻነት የቀረበውን ክርክር የሚመለከት ነው፡፡ ክርክሩ የተጀመረው በቀበሌ ማህበራዊ ፍ/ቤት ሲሆን ከሣሽ የነበረውም የአሁኑ አመልካች ነው፡፡ በተጠሪ ላይ ክስ የመሰረተው ከቀበሌ ተከራይቼ የምኖርበትን ቤት ማእድ ቤት ለማደስ ያደረግሁት እንቅስቃሴ እንዳይሳካ ሁከት ስለፈጠረችብኝ ሁከቱ ይወገድ ዘንድ ይታዘዝልኝ በማለት ነው፡፡ ማህበራዊ ፍ/ቤቱ ተጠሪን በማስቀረብ ክርክሩን ከሰማ በኂላ የአመልካችን ክስ ውድቅ በማድረግ ወስኗል፡፡ በሌላ በኩል ደግሞ አመልካቹ ውሳኔውን በመቃወም ለአዲስ አበባ ከተማ አስተዳዳር የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት ይግባኝ በማቅረቡ ክርክሩ እንደገና ተሰምቷል፡፡ በመጨረሻም ፍ/ቤቱ በማህበራዊ ፍ/ቤት የተሰጠውን ውሳኔ በማጽናቱ አመልካች አሁንም ለአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ይግባኝ ሰሚ ፍ/ቤት የሰበር አቤቱታ አቅርቦ ክርክሩ እንዲሰማ አድርጓል፡፡ ፍ/ቤቱም ክርክሩን ከመረመረ በኂላ በአብላጫ ድምጽ በሰጠው ውሳኔ በስር ፍ/ቤቶች የተሰጠውን ውሳኔ አጽንቷል፡፡ የአሁኑ አቤቱታ የቀረበው በዚሁ ላይ ነው፡፡

በበኩላችንም አመልካች የካቲት 5 ቀን 2000 ዓ.ም በጻፈው ማመልከቻ ያቀረበውን አቤቱታ መሰረት በማድረግ ክርክሩን ሰምተናል፡፡ አቤቱታው በሰበር ችሎት እንዲታይ የተወሰነው ጉዳዩ በቀበሌ ማህበራዊ ፍ/ቤት የዳኝነት ስልጣን ስር የሚወድቅ ስለመሆን አለመሆኑ ለመመርመር ነው፡፡ በመሆኑም ይህን ነጥብ ከግራ ቀኝ ወገኖች ክርክር፣ አቤቱታ ከቀረበበት ውሳኔ እና ከሕጉ ጋር አገናዝበን መርምረናል፡፡

ከላይ እንደተገለጸው አመልካች ለቀበሌ ማህበራዊ ፍ/ቤት ክስ ያቀረበው ተጠሪ የማእድ ቤቱ እድሳት እንዳይካሄድ በመከልከል የፈጸመችው ድርጊት ሕገ ወጥ ነው ተብሎ እንዲወገድ እና እድሳቱን እንዲያካሂድ እንዲወሰንለት በመጠየቅ ነው፡፡ የክሱ ምክንያት ሕገ ወጥ ነው የተባለው ድርጊት እንዲወገድ የሚጠይቅ ከመሆን አልፎ የገንዘብ ጥቅም ወይም በገንዘብ ሊተመን የሚችል መብት የሚጠይቅ አይደለም፡፡ ጉዳዩ በቀበሌ ማህበራዊ ፍ/ቤት የዳኝነት ስልጣን ስር የሚወድቅ ነው ወይ? የሚል ጥያቄ ሊነሳ የቻለውም በዚህ ምክንያት ነው፡፡

በግልጽ እንደሚታወቀው ማንኛውም ፍ/ቤት አንድን ጉዳይ ተቀብሎ ሊያስተናግድ የሚችለው በክልልም ሆነ በስረ-ነገር ረገድ የዳኝነት ስልጣን ሲኖረው ነው፡፡ የስረ-ነገር የዳኝነት ስልጣንን በሚመለከትም ሕጉ ጥብቅ የሆነ ድንጋጌ አስቀምጦአል፡፡ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁ.9/1/ እንደተመለከተው በስረ-ነገሩ ለመዳኘት ስልጣን የሌለው ፍ/ቤት የክስ ማመልከቻውን በፍ/ብ/ሕግ ቁ.231 በተደነገገው መሰረት ተቀባይነት የለውም ብሎ መመለስ አለበት፡፡ ፍ/ቤቱ ይህን እርምጃ መውሰድ ያለበት ተከራካሪ ወገን መቃወሚያ እንዲያቀርብለት ሳይጠብቅ በራሱ አነሳሽነት እንደሆነም በዚሁ ቁ.9/2/ በግልጽ ተመልክቶአል፡፡ በመሆኑም በዚህ ድንጋጌ የተቀመጠውን አስገዳጅ መርህ ለማስከበር ሲባል የቀበሌ ማህበራዊ ፍ/ቤቱ በጉዳዩ ላይ የስረ-ነገር የዳኝነት ስልጣን ነበረው ወይ? የሚለው ጭብጥ መያዙ ተገቢ ነው፡፡

በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር በየቀበሌው የቀበሌ ማህበራዊ ፍ/ቤቶች እንዳሉና የመዳኘት ስልጣንም እንደተሰጣቸው በተሻሻለው የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ቻርተር አዋጅ ቁ. 361/95 አንቀጽ 39 ተመልክቷል፡፡ የፍ/ቤቶቹን የስረ-ነገር የዳኝነት ስልጣን በተመለከተ በሚደነግገው የአዋጁ አንቀጽ 50/1/ እንደተመለከተውም ግምታቸው ከብር 5000(አምስት ሺ.ህ) ባልበለጡ የንብረትና የገንዘብ ክርክሮች ብቻ የተወሰነ የስረ-ነገር የዳኝነት ስልጣን ነው ያላቸው፡፡ በያዝነው ጉዳይ እንደምናየው ለክርክሩ መነሻ የሆነው ክስ በገንዘብ የሚተመን አይደለም፡፡ በገንዘብ የማይተመኑ ወይም የገንዘብ ግምት የሌላቸው፣ ነገር ግን መሰረታዊ የሆነ የመብት ጥያቄ የሚያስነሱ ክሶች የሚታዩበትን ሁኔታ ሕጉ በተለየ ሁኔታ ደንግጓአል፡፡ በቀበሌ ማህበራዊ ፍ/ቤቶች የስረ- ነገር የዳኝነት ስልጣን ስር እንዲወድቁ ግን አልደነገገም፡፡ የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ይግባኝ ፍ/ቤት ሰበር ችሎት አነስተኛ ድምጽ የቀበሌ ማህበራዊ ፍ/ቤቱ የስረ-ነገር የዳኝነት ስልጣን የለውም በማለት ከአብላጫው ድምጽ የተለየውም በዚህ ምክንያት እንደሆነ ለመገንዘብ ችለናል፡፡ በበኩላችንም ትክክለኛ ሆኖ ያገኘነው በአነስተኛው ድምጽ የተሰጠው የሕግ ትርጉም ነው፡፡ ከዚህ የተነሣም በአብላጫው ድምጽ የተሰጠው ውሳኔ መሰረታዊ የሕግ ስህተት ያለበት ነው ለማለት ችለናል፡፡

## ው ሳ ኔ

1. በቀበሌ ማህበራዊ ፍ/ቤት እና በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት በመ/ቁ. 02188 ታሕሣሥ 3 ቀን 1998 ዓ.ም ተሰጥቶ በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ይግባኝ ፍ/ቤት ሰበር ችሎት በመ/ቁ. 02897 ታሕሣሥ 25 ቀን 2000 ዓ.ም በተሰጠው ውሳኔ የፀናው ውሳኔ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁ. 348/1/ መሰረት ተሽሯል፡፡
2. ጉዳዩ በቀበሌ ማህበራዊ ፍ/ቤት የዳኝነት ስልጣን ስር የማይወድቅ በመሆኑ ማህበራዊ ፍ/ቤቱ ክሱን ያስተናገደው ከሕግ ውጪ ነው በማለት ወስነናል፡፡
3. ወጪና ኪሣራ በሚመለከት ግራ ቀኝ ወገኖች የየራሳቸውን ይቻሉ፡፡ መዝገቡ ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ቤ/ኃ